
ספריית פיג'מה לקטנטנים

# የድብብቆሽ ጨዋታ

**ከታዳጊ ህጻናት ጋር ማንበብ**

በቀላልና አዝናኝ ጨዋታ ውስጥ በጣም ብዙ ነገር ይከሰታል፡- እንዝናናለን የማወቅም ጉጉት አለን - አባዬ የት አለ? አሁን ምንድን ነው የምናደርገው? - ለአዲስ ሁኔታ መፈለግና መፍትሔ ማግኘትን እንማራለን። አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር ባናያቸውም እንኳን ስናገኛቸው የምስጢር መፍትሔው በስኬትና በደስታ ስሜት ይሞላናል - አባዬ አልጠፋም! አግንተነዋል!



**በድብብቆሽ መጫወት**

ኑ ድብብቆሽ እንጫወት! ጣቶቻችንን በእጅ መዳፍ ውስጥ መደበቅ፣ አፍንጫችንን ሸፍነን መግለጥ፣ በብርድ ልብስ መደበቅ፣ ከሶፋው ጀርባ መደበቅ ወይም አሻንጉሊትን ከጀርባ መደበቅ እንችላለን።

*መጀመሪያ መደበቅ የሚፈልገው ማነው?*

**ድመቱን ፈልጉ**

ሜያው! ግራጫው ድመት የድብብቆሽ ጨዋታውን ተቀላቅሏል። በእያንዳንዱ ስዕላዊ መግለጫ ላይ እርሱን መፈለግ ይቻላል፤ ጅራቱን እንዳትረግጡ ብቻ ተጠንቀቁ ...

**ለንባብ ጠቃሚ ምክር፡- መጽሐፉን ወደ ጓደኛ እንዴት ይለውጡታል?**

ከትንሽነታቸው ጀምሮ መጻሕፍትን ማንበብ ለታዳጊ ህፃናት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። ነገር ግን በሁሉም አዲስ ነገር ላይ ጥያቄ እንደሚነሳው ሁሉ - መንገዱን እንዴት እናገኘዋለን? የእኛ ሀሳብ በዝግታና ቀስ በቀስ መተዋወቅ ነው - ታዳጊው በራሱ መንገድ ከመጽሐፉ ጋር መገናኘት ይችላል፡- በመንካት፣ በመክፈትና በመዝጋት እና በአፍ ውስጥ እንኳን "መቅመስ" ሳይቀር። ከዚያ ማንበብ ይችላሉ፡- በየቀኑ ትንሽ በትዕግስትና በደስታ እናነባለን። መጀመሪያ ላይ አንድ ገጽ እንኳን ማንበብ፣ መተዋወቅና መለማመድ ይችላሉ። እነሆ - መጽሐፉ ጓደኛ ሆኗል!

የQR ትርጉምና በላዩ ላይ ይፃፉ - Pyc / Eng / አማር

**የQR ኮድ -** የፒጃማ ቤተ መፃህፍት በማንኛውም እድሜ የሚሆን የጋራ የንባብ እድል